# የጸረ ሽብር አዋጁ የመድብለ ፓርቲ ስርዓቱን የበለጠ የሚያጠናክር ነው

እልፍነሽ ጽጌ 08/27/13

የዓለም ህዝብ በአሁኑ ወቅት ከተጋረጡበት ዋነኛ ፈተናዎች መካከል የተለያየ የፖለቲካ አስተሳሰብን የሚያራምዱ አካላት ዓላማዎቻቸውን ለማስፈጸም ተጽእኖ ይፈጥርልናል በሚል የሚፈጽሙት የሽብር ተግባር አንዱና ምናልባትም ቁልፉ መሆኑን ብዙዎች ይናገራሉ፡፡ ይህ ተግባር የሚፈጸመው ንጹሃንና ራሳቸውን ለመከላከል አንዳችም አቅም በሌላቸው የሰው ፍጡራን ላይ ከመሆኑ ባሻገር እጅግ በረቀቀ ሚስጥርና በህቡእ በሚንቀሳቀሱ አካላት መሆኑ ደግሞ ችግሩን እጅግ አደገኛና ዘግናኝ ያደርገዋል፡፡

በዚህ ኢሰብአዊነት በተጠናወተው ተግባር በዋነኝነት የተጠቁትና አሁንም ድረስ ፋታ ያላገኙት አገራት አሜሪካንን ጨምሮ ታላላቅ የምእራብ አገራትና የመካከለኛው ምስራቅ ክፍለ አህጉር ቢሆኑም የእነዚህኑ አገራት ዱካ በመከተልም የአፍሪካ አገራትም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሰለባ የሆኑበት አጋጣሚ በርካታ ነው፡፡

አገራችን ኢትዮጵያም እላይ ከተጠቀሰው በተለየ መንገድ በሽብር ሴራ ክፉኛ የተጠቃች አገር ሆና መቆየቷም ገሃድ የወጣ እውነት፡፡ ለፖለቲካ ስልጣን እንታገላለን በሚል ጦር አንግበው በሚንቀሳቀሱ ጥቂት አማፂያን አማካኝነት በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በተፈፀሙ የሽብር ሴራዎች በመቶዎች የሚቆጠር ህይወት ከመጥፋቱም ባሻገር በሚሊዮኖች የሚገመት ንብረት ወድሟል፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ በተለይ ሽብር በሚፈፀምባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ ህዝቦችን የእለት ተእለት ህይወት በስጋትና ፍርሃት እንዲሞላ ከማድረግ በተጨማሪ አገሪቱ የጀመረችውን የሰላም፣ የእድገትና ለውጥ መንገድ በተወሰነ መልኩም ቢሆን ለማደናቀፍ ሞክረዋል፡፡

የተባበሩት መንግስታትን ጨምሮ የዓለም አገራት በአሁኑ ወቅት የፀረ ሽብር ህግ አውጥተዋል፡፡ ኢትዮጵያም የዚህ የጥፋት ተግባር ሰለባ ከመሆን ባለፈ የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ አካል በመሆኗ የዛሬ አራት ዓመት ገደማ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀና የህዝቦችን ሰላምና መረጋጋት

እንደዚሁም የአገሪቱን እድገት ቀጣይነት ሊያረጋግጥ የሚችል የጸረ ሽብር ህግ አውጥታ መተግበር ጀምራለች፡፡

ሆኖም ግን አንዳንድ የአገሪቱ ተቃዋሚዎች ይህ ህግ አልተዋጠላቸውም፡፡ እነዚህ ተቃዋሚዎችና አንዳንድ የውጭ አጋሮቻቸው ይህንን ህግ ለምን ይቃወሙታል የሚል ጥያቄ አለኝ፡፡ እነዚህ አካላት ኢትዮጵያ የፀረ ሽብር ሕግ አያስፈልጋትም በማለት ሲሞግቱ አራት ዓመታት አልፈዋል፡፡ ተቃዋሚዎች ሕጉ ከወጣ በኋላ የሀገሪቱ ሕዝቦች የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ጥሷል፤ ዜጎችም በፍርሃት ድባብ ውስጥ እንዲሆኑና ጋዜጠኞችና የፖለቲካ አመራሮች መታሰራቸውን በመግለጽ ይከሳሉ፡፡

በኢትዮጵያ መላው ህዝብ በመከላቸው አካላት በ1997 ዓ.ም ፀድቆ ስራ ላይ የዋለው ህገ መንግስትና ይህንንም ተከትሎ የተመሰረተው ፌደራላዊ የፖለቲካ ስርዓት በአገሪቱ ህዝቦች ብዙ መቶ ዓመታት ሲከባለሉ የኖሩትንና የዜጎችን ህይወት በሰቆቃ አጨናንቀው ለነበሩት የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ችግሮች ማብቂያ ያበጀ ስለመሆኑ በአሁኑ ወቅት የሚታዩትን ለውጦች ብቻ በማየት መመስከር እንደሚቻል የብዙ ታዛቢዎች እምነት ነው፡፡

የኢትዮጵያ ህዝቦች በማንነታቸው ኮርተው ከመቆም ባሻገር የፖለቲካ ስልጣን ባለቤት ሆነዋል፡፡ መቼም ሊያደርጉት ቀርቶ ሊያስቡት ይሳናቸው የነበረውን መሪር እውነታ በመገርሰስ መሪዎቻቸውን በራሳቸው ይሁንታ ማረጋገጥ የቻሉበት የምርጫ ስርዓት ባለቤት ሆነዋል፡፡

የፖለቲካ ስርዓቱ የህዝብን የመወሰን አማራጭ በማስፋት የአገሪቱን ሁለንተናዊ ሁኔታ ማጎልበት የሚያስችል የመድብለ ፓርቲ ስርዓትን የገነባ በመሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች በህጋዊና በሰላማዊ መንገድ የሚታገሉበትን ሁኔታም ፈጥሯል፡፡ በዚህም የተነሳ እጅግ በርካታ ሊባሉ የሚችሉ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ህጋዊ እውቅና ተሰጥቷቸው ያለምንም ገደብ በመንቀሳቀስ ላይ ናቸው፡፡ እነዚህ ፓርቲዎች በየአራት አመቱ በሚካሄደው አገራዊ ምርጫ ላይም በመሳተፍ ላይ ይገኛሉ፡፡

በመሆኑም የአገሪቱ ብሄር ብሄረሰቦች በሚኖሩበት ክልል በሚመለከቷቸው ጉዳዮች መወሰንና ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር ከመቻላቸው ባለፈ በአገሪቱ በሚካሄዱት ምርጫዎች ከሚሳተፉት የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የሚበጃቸውን በነጻነትና በታላቅ ተሳትፎ በመምረጥ የዴሞክራሲ ስርዓትን ማጣጣም ችለዋል፡፡

ይህ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ስርዓት የፈጠረውን ይህንን ምቹ ሁኔታ ተከትሎም ለአያሌ ዓመታት በቅሬታ፣ በመጠራጠርና በጠላትነት እየተያዩ ከመነጣጠል ውጭ ሌላ አማራጭ ጠፍቷቸው የነበሩት የአገሪቱ ህዝቦች በአሁኑ ወቅት እጅግ ከመቀራረብ አልፈው በመከባበር ላይ የተመሰረተ አንድነትን ተጎናፅፈዋል፡፡ ይህም በአገሪቱ ታይቶ የማይታወቅ የኢኮኖሚ እድገትንና ለሌሎች አርአያ ሊሆን የሚችል ሰላምና መረጋጋትን እውን አድርጓል፡፡

በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ እውነትና ተጨባጭ ነው፡፡ በተለያዩ ወቅቶች በተካሄዱ ዓለም አቀፉ ጉባኤዎች ላይ የሚነገረውም ይህ ነው፡፡ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ኢኮኖሚ ሁኔታ በቅርበት የሚከታተሉ የውጭ አገራትና ኢትዮፕያዊያን ምሁራን እንደዚሁም የተለያዩ አገራት የፖለቲካ ሰዎችና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተመራማሪዎች በኢትዮጵያዊ  አሁን ስራ ላይ የዋለው የፖለቲካ ስርዓት ባይፈጠር ኖሮ ዛሬ ይህች አገር የደረሰችበትን ደረጃ መጎናጸፍ አይቻላትም ነበር የሚል ትንተና አቅርበዋል፡፡

በከፋ ድህነት ብቻ ትታወቅ በነበረችው አገራችን ዛሬ የሚስተዋለው ድህነትን የማሸነፍ ጦርነት፤ ይህንንም ጦርነት በድል ለመወጣት በህዝቡ ውስጥ የሚንፀባረቀው ከፍተኛ መነቃቃት መላውን ዓለም ያስደመመ ስለመሆኑ ብዙ ተብሏል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአገሪቱ በአሁኑ ወቅት ያለው ሰላምና መረጋጋት የሌሎች አፍሪካ አገራት ምሳሌ ሆኖ መቅረቡና አገሪቱ በተለይ በአፍሪካ ሰላምና መረጋጋትን ማምጣት የምትችል አገር ተደርጋ መነሳቷ የስርዓቱ ነጸብራቆች መሆናቸውን በሙሉ ልብ መናገር ይቻላል፡፡

ከዚህም የኢትዮጵያ የዛሬ እውነታ አኳያ በአሁኑ ወቅት በዚህች አገር ያለው የፖለቲካ ኢኮኖሚ ዜጎች ጥያቄዎቻቸውን ማቅረብና ምላሽ ማግኘት የሚችሉበት ነው፡፡ በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል ቅሬታ ሊፈጠር ይችላል፤ ሆኖም ግን ይህ ቅሬታ በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ለመመለስ የሚያስችል ስርዓት ተተክሏል፡፡

በመሆኑም በአሁኑ ወቅት ጠብመንጃ አንግቦ ወደጫካ ሊያስከባ የሚችል አንዳችም ምክንያት የለም፡፡ ለህዝብና ለአገር የሚጠቅም የተለየ የፖለቲካ አስተሳሰብ አለን የሚሉ ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ቢሆኑ ይህንን ዓላማቸውን በነጻነት የመስበክ ብሎም በየአራት ዓመቱ በሚካሄደው ምርጫ ላይ በመሳተፍ ዓላማቸውን ከግብ የሚያደርሱበት መሰረት ተጥሏል፡፡

ባለፉት ስርዓቶች የጭቆና አገዛዝ የህዝብ ምሬት የሆኑት ቁልፍ የዴሞክራሲና የልማት ጥያቄዎች በአሁኑ ስርዓት ህገ መንግስታዊ መሰረትን ተጎናጽፈው ምላሽ የተሰጣቸው ጥያቄዎቹ ሞተው ከተቀበሩ ሁለት አስርት ዓመታት አልፈዋል፡፡ ይህ በማንም ሊስተባበል የማይችል እውነት ሆኖ ሳለ ግን ጥቂት የፖለቲካ ቡድኖች ይህንን እውነት መቀበል ተስኗቸው ይስተዋላል፡፡ የፖለቲካ ጥያቄዎቹ የሞቱና ያለቀላቸው በመሆኑ መፈናፈኛ ያጡ ጥቂት ኃይላት በዴሞክራሲያዊው ስርዓት ውስጥ አልፎ ስልጣን መያዝ ስለተሳናቸው ሌላ የጥፋት አማራጭን ይዘው ሲንቀሳቀሱ ይታያል፡፡

በተለያዩ ወቅቶች በተካሄዱ ምርጫዎች ላይ የህዝብ ይሁንታ ያጡትን ጨምሮ ሌሎችንም ያካተተው ይህ ጎራ በምርጫ ያጣውን ስልጣን ዴሞክራሲያዊ ስርዓቱ የፈጠረውን መብት በመጠቀም ጭምር በኃይልና ጸረ ህገ መንግስታዊ በሆነ መንገድ ለማሳካት ይታትራል፡፡

ይፋዊ በሆነ መልኩ የትጥቅ ትግል ውስጥ የገቡትን ኦነግና ኦብነግ የመሳሰሉትን ጨምሮ በአገሪቱ የተዘረጋውን የዴሞክራሲ ስርዓት ተገን በማድረግ በህቡእ ውስጥ ውስጡን ህገ ወጥ የሆኑ ተግባራትን የሚፈጽሙ የፖለቲካ ፓርቲዎች መኖራቸው በተለያዩ ወቅቶች ገሃድ የወጣ ሀቅ ነው፡፡ በይፋ የሚታወቁት ጸረ ሰላም ኃይሎችን ጨምሮ በፖለቲካ ፓርቲና በነጻ ፕሬስ ስም በዚሁ ዓይነት ክፉ ተግባር ተጠምደው የአገርን ሰላምና ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ወንጀል ስለመፈጸማቸው የመገናኛ ብዙሃን በተለያዩ ወቅቶች ዘግበው ሰምተናል፡፡

በተለይ ይፋዊ በሆነ መንገድ **የትጥቅ ትግል ውስጥ ነን** የሚሉት ኦብነግንና ኦነግን የመሳሰሉ ሽብርተኛ ቡድኖች በተለያዩ ወቅቶች በአገሪቱ ንጹሃን ዜጎች ላይ ለደረሱት አደጋዎች በይፋ ኃላፊነታቸውን የወሰዱባቸው አጋጣሚም በርካታ ናቸው፡፡ ከዚህም ሌላ በአገር ውስጥ ዴሞክራሲው ያጎናጸፋቸውን መብት ተገን በማድረግ ግንቦት ሰባት ከተባለው የጥፋት ቡድን ጋር በህቡእ በመቀናጀት ሊፈጸሙ የሚችሉ የተለያዩ የጥፋት ተግባራትም ተደርሰባቸው መክነው መቅረታቸውንም ሰምተናል፡፡

የጥፋት ቡድኖቹ የተጠናወታቸውን የስልጣን ጥም ለማሳካት ሲሉ የኢትዮጵያ ሰላምና እድገትን ከማይሹ የውጭ ኃይላት ጋርም አብረው በመንቀሳቀስ ላይ መሆናቸውም ገሃድ የወጣ እውነት ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ሻእቢያንና በሶማሊያ ይንቀሳቀስ የነበረውን አልሸባብ ማንሳት ይበቃል፡፡

የሆነው ሆኖ ግን ህዝብ ይሁንታ ያልሰጠው ምንም ዓይነት ተግባር ሊሳካ እንደማይችል የሚታወቅ በመሆኑ የእነዚህ ቡድኖች ምኞች ብዙ ርቀት አልሄደም፡፡ በስርዓቱ አማካኝነት የኢትዮጵያ ህዝብ ጥያቄዎቹ የተመለሱለትና ሁለንተናዊ ተጠቃሚነቱንም እያጣጣመ በመሆኑ ለእንደነዚህ ዓይነቶቹ

የጥፋት ኃይሎች እንዳችም ድጋፍ እየሰጠ አይደለም፡፡ በአሁኗ ኢትዮጵያ ለዚህ ዓይነቱ የጥፋት ተግባር ሊጋብዝ የሚችል እንዳችም ዓይነት ተጨባጭ ምክንያትና እውነት የሌለ መሆኑን ህዝቡ ለእንደዚህ ዓይነቶቹ ቡድኖች ከነፈገው ድጋፍ መረዳት ይቻላል፡፡ ለዚህ ብዙ ማሳያዎችን ማቅረብ ይቻላል፡፡

እነዚህ ቡድኖች እንታገልለታለን ለሚሉት ባዶ ዓላማ ሲንቀሳቀሱ ብዙ ዓመታትን ያስቆጠሩ ቢሆንም እንዳችም ፋይዳ ያለ ውጤት አላመጡም፤ እንዲያውም በአሁኑ ወቅት እየተከፋፈሉ በከፍተኛ ደረጃ በመዳከም ላይ ናቸው፡፡ ተግባሩ የማያዋጣቸው መሆኑን የተገነዘቡ አባላቶቻቸውም የትጥቅ ትግሉን በማቋረጥ ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ውስጥ መቀላቀል ጀምረዋል፡፡

እንዲያም ሆኖ አሁንም ድረስ የዚህ ዓይነቱ የጥፋት ሴራ እንደቀጠለ ነው፡፡ በህጋዊ መንገድ የተደራጁ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጭምር ሊኖሩበት የሚችል የጥፋት ሴራ የኢትዮጵያን ሰላምና እድገት ከማይመኙ የውጭ ኃይላት ጋር በመተባበር ሊፈፀም እንደሚችል መገመት አያዳግትም፡፡

ለዚህ ግምት ማጠናከሪያ ሊሆን የሚችለው የቅርብ ጊዜ ክስተት ኢትዮጵያ ከታላቁ የህዳሴ ግድብ ጋር በተያያዘ ከግብጽ አክራሪ የፖለቲካ ቡድኖች ጋር ማበር የጀመረውን ግንቦት ሰባት የተሰኘ የሽብር ቡድን ማንሳት ይቻላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በመካከለኛው ምስራቅና በሰሜን አፍሪካ አንዳንድ አገራት ውስጥ ተከስቶ የነበረውን ዓይነት ህዝባዊ ቀውስ ወደአገራችን እንዲዛመት የተደረጉትና አሁንም ድረስ እየተደረጉ ያሉት የጥፋት ዘመቻዎችንም ከዚህ አኳያ ማውሳቱ ተገቢ ይመስለኛል፡፡

እነዚህ ተቃዋሚዎችና አንዳንድ የውጭ አጋሮቻቸው ይህንን ህግ ለምን ይቃወሙታል በሚል እላይ ላነሳሁት ጥያቄ ከላይ የተነሱት እውነታዎች ከፊል መልስ ይሆናሉ የሚል እምነት አለኝ፡፡ በአገሪቱ ህግ መሰረት በሽብር ጥቃትና ሴራ ውስጥ መሳተፋቸው በራሳቸው ሰዎች ጭምር በአደባባይ ተረጋግጦ ጥፋተኛ ሆነው በመገኘታቸው እስር የተፈረደባቸውን የፖለቲካ አጋሮቻቸውንና ይህንን የሚያራምዱላቸውን ጋዜጠኛ ተብዬዎች መታሰርን በመግለጽ ነው አዋጁን የሚቃወሙት፡፡

እንደእኔ እምነት በአሁኑ ወቅት በአገራችን አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚጠሯቸው የተቃውሞ ሰልፎች፣ ህዝባዊ ስብሰባዎችና በአመራሮቹ የሚሰጡት ተከታታይ መግለጫዎች በአገሪቱ ሁከት እንዲፈጠር ያለሙ ናቸው፡፡

እነዚህ የተቃውሞ ሰልፎች ላይ የሚነሱት ሀሳቦችና የሚስተጋቡት መፈክሮች ኢ-ዴሞክራሲያዊና ህገ ወጥ መሆናቸውን በብዙ መልኩ እየታዘብን ነው፡፡

በተለይ የጸረ ሽብር ህጉ እንዲሰረዝ ሲሉ የጀመሩት ዘመቻ ዓላማ የሚፈልጉትን የፖለቲካ ስልጣን የመጨበጥ ህልም ያሳካልናል የሚሉትን ህዝባዊ አመጽ ማነሳሳት፣ ህዝብና ህዝብን በደም ማቃባት ከመሆን ውጭ ሌላ ሊሆን አይችልም፡፡

ይህ ደግሞ በፀረ ሽብር አዋጁ ተዘግቷል፡፡ የጸረ ሽብር አዋጁን የተቃወመ አስተሳሰብ ላይ በማተኮር በአሁኑ ወቅት በአንዳንድ የተቃዋሚ ቡድኖች በቅንጅት የተጀመረው እንቅስቃሴ ዓላማ በአዋጁ ይበልጥ የተጠናከረውን ህጋዊውን የመድብለ ፓርቲ ፖለቲካ ለመቀልበስ ዘውትር ሲያልሙት የኖሩትን ህገ ወጥ የሆነ መንገድ የዘጋ መሆኑን በመገንዘባቸው ነው ብዬ በሙሉ ልብ አምናለሁ፡፡

አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና የፖለቲካ ኢኮኖሚ ርእዮታቸውን በኢትዮጵያ ላይ ለመጫን ከፍተኛ ጉጉት ያላቸው የውጭ ኃይላት በአገራችን የተተከለውን የመድብለ ፓርቲ ስርዓት መናድ እንደማይችሉ አዋጁ አረጋግጧል፡፡